# የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የመድን ውልና የካሣ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 767/2013 (ማሻሻያ)

Insurance Fund Management Agency Vehicle Accident Third Party Insurance Insurance Contract and Compensation Implementation (Directive No. 767/2013) (Amendment)

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
MINISTRY OF TRANSPORT AND LOGISTICS

መጋቢት 7፥ 2013

## የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የመድን ውልና የካሣ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 767/2013

## /ማሻሻያ/

የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን የመድን ውልና የካሳ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 3/2010 የወጣውን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 29(2) እና በመመሪያው አንቀጽ 40 መሠረት እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   - ይህ መመሪያ የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የመድን ውልና የካሳ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 767/2013 "ማሻሻያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

   - የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የመድን ውልና የካሣ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 3/2010 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

     1. የመመሪያው አንቀፅ 10(4) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 10(4) ተተክቷል፡፡

        10(4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ (2) እ.ኤ.አ. (Gregorian calendar) የቀን አቆጣጠር የተቀመጠው የአንድ ወር ጊዜ ካበቃ በኋላ ባለው 5 የስራ ቀናት ውስጥ ለመድን ገቢዎች የሠጠውን የመድን ምስክር ወረቀት እና የመድን ተስጣፊ ብዛት እና ዝርዝር መረጃ ሲዘጋጁ በመበላሸታቸው የተሠረዙ ሠነዶችን እና የተከፈለ ካሣ፣ በሒደት ላይ ያለካሣ መጠንና ብዛት ከሪፖርት ጋር አያይዞ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡

     2. የመመሪያው አንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ 2 ተተክቷል፡፡



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport

11(2) ለፈንድ ገቢ አሰባሰብ ሲባል የሂሳብ ዘመኑ የሚሆነው ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ቀን ሲሆን እያንዳንዱ የሂሣብ ዘመን ለ12 ወራት የሚከፈል ነው ፡፡

3. የመመሪያው አንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ (3) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ (3) ተተክቷል፡፡

11(3) ማንኛውም መድን ሰጭ የሚሰበሰበው የፈንድ መጠን እያንዳንዱ ወር ባለቀ በሚቀጥለው ወር የመጨረሻ ቀን ድረስ ለኤጀንሲው ገቢ ማድረግ አለበት፣ የቀጣዩ ወር የመጨረሻ ቀን ዕሁድ ወይም የበዓል ቀን ከዋለ በቀጣዩ የስራ ቀን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

4. በመመሪያው አንቀጽ 11 ስር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ-አንቀጽ (9) እና (10) ተጨምረዋል፡፡

11(9) ማንኛውም መድን ሰጭ የሰበሰበው የፈንድ መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11(3) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካላስገባ ክፍያውን ላዘገየበት ጊዜ የዘገየው የገንዘብ መጠን ላይ በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ የተደነገገውን ህጋዊ ወለድ ጨምሮ የሰበሰበውን ፈንድ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

5. በመመሪያው አንቀፅ 11 ስር አዲስ ንኡስ አንቀፅ (10) ተጨምሯል

11(10) የሰበሰበውን ፈንድ ለሁለት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ የሚያዘገይ የመድን ሰጭ ኩባንያ የተቀመጠውን የክፍያ ጊዜ ጠብቆ ገቢ እንዲያደርግ ኤጄንሲው በፁሁፍ ያሳውቀዋል፡፡ የማያሻሽል ከሆነም በአዋጁ አንቀፅ 30 መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 3. የመመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

- ይህ መመሪያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ዳግማዊት ሞገስ

የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር